MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland

# Superintendent ስላቀረበው የ2016 በጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀት ፈጣን እውነታዎች

ዲሰምበር 2014

የMONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS (MCPS) Superintendent Joshua P. Starr ለ2016 በጀት ዘመን (የ2015-16 የትምህርት አመት) የ$2.4 ቢልዮን የስራማስኬጃ በጀት አቅርቧል። ይህ ከወቅታዊው ስራ ማስኬጃ በጀት (2015 በጀት ዘመን) ላይ 4.6 በመቶ ($103.6 ሚልዮን) ጭማሪ ነው። $23.3 ሚልዮን ተጨማሪ የካውንቲው ምክርቤት በ2015 በጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀት ይጠቀምበት የነበረውን፣ የጡረተኛ ጥቅሞችን የሚሸፍን ሂሳብ የሚያካትት፣ ያንድ-ጊዜ ምንጮችን ለመተካት ይፈለጋል። በተጨማሪ፣ ምክር ቤቱ ከ2014 በጀት ዘመን ተጠቅሞበት የነበረውን ከMCPS ትርፍ ገንዘብ ለመተካት $22 ሚልዮን መስጠት ይኖርበታል።

የ2016 የበጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀት ከበርካታ አመት በጀታዊ ስልት ሶስተኛው አመት ሆኖ ስልቱም MCPS የሚከተሉትን ለማከናወን የሚያስችሉ የተወሰኑ የሙአለንዋይ ፈሰሶች ያደርጋል፡-

- ቀጣይ እድገቶቹን ለማስተዳደር፤
- የግኝት ክፍተቶችን ለማጥበብ፣ ብሎም ለመዝጋት፤ እና
- ተማሪዎችን ለወደፊት ለማዘጋጀት ፈጠራዊነትን መንከባከብ።

## እድገትንና ተጨማሪ ወጪዎችን ማስተዳደር

አብዛኛው ጭማሪ በDr. Starr የቀረበው በጀት ባጭሩ MCPSን እያደገ ለሚመጣው የተማሪዎች ቁጥር—ከ2,000 በላይ በእያንዳንዱ አመት ባለፉት ሰባት አመቶች—ተመሳሳይ አገልግሎቶች እንዲያቀርብ ለማስቻል ነው። ይህም የሚያካትተው ከ270 በላይ የስራ ቦታዎች የምዝገባ እድገትን ለመቋቋም ብቻ፣ ከነዚህም 111 የኤሌሜንታሪ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የስራ ቦታዎች፣ 96 የልዩ ትምህርት የስራ ቦታዎች፣ 41.5 የስራ ቦታዎች ከእንግሊዘኛ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች (English for Speakers of Other Languages (ESOL)) አገልግሎቶች የሚቀበሉ ተማሪዎችን ለማገልገል፣ እና 25 የስራ ቦታዎች ለትራንስፖርት ያጠቃልላሉ።

ጭማሪው ቀጣይ ወጪዎችንም ይሸፍናል፣ ለMCPS ሰራተኞች ማካካሻ ጭማሪ፣ ለወቅታዊ ሰራተኞችና ጡረተኞች ጥቅማጥቅሞች፣ የትራንስፖርትና የስራ እንቅስቃሴ ወጭዎች፣ አቅርቦቶች፣ ቁሳቁሶች፣ እና ተኤክኖሎጂን ጨምሮ። በDr. Starr ወጭዎችን በመቆጣጣር በሚገኝ ቁጠባ፣ በበጀት በመቆረጥ፣ እና ሰራተኞች ለጤና ጥቅሞች በሚያደርጉዋቸው አስተዋፅኦዎች የተወሰነ የበጀት ጭማሪ ሊካካስ ይችላል።

## ስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰስ

DR. STARR $8.2 ሚልዮን የተለመው የግኝት ክፍተትን በማጥበብና ተመሪዎችን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ያተኮሩ ስልታዊ ተቀዳሚ ማሻሻሎች በማቅረብ ላይ ይገኛል ከሙአለንዋይ ፈሰሶች በከፊል—

- 18 አማካሪዎች፣ የት/ቤት ሳይኮሎጂስቶች፣ እና ተማሪ የፔርሶኔል ሰራተኞች (pupil personnel workers) በዲስሪክቱ ከዳር እስከዳር በማዳረስ የተማሪ አገልግሎት ሞዴልን ለማሻሻል ጥረቶችን ለመቀጠል $1.5 ሚልዮን፤
- በዲስትሪክቱ በሞላ የሚገኙትን የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማሻሻል ጥረቶች፣ 6.8 የስራ ቦታዎችን ጨምሮ፣ $1 ሚልዮን፤
- የሙአለንዋይ ፈሰስ በLearning and Academic Disabilities (መማርና አካዴሚያዊ ስንክልና) አገልግሎቶች በኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች፤ የኤሌሜንታሪ ተማሪዎችን በአካባቢያቸው ት/ቤት ውስጥ አገልግሎት የመስጠት ጥረቶች፤ እና ለተማሪዎች ወቅታዊ አገልግሎቶች የሚደገፈውን የHigh Incidence Accessible Technology (HIAT) ቡድን አጠቃቀም ማስፋፋትን የሚያካትት ስንክልና ያላቸውን ተማሪዎች አገልግሎት ለማሻሻልና ድጋፍ ለመስጠት $1 ሚልዮን (12 የስራ ቦታዎች)፤
- በኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች የሂሳብ ግንዛቤና ግኝት ለማሻሻል አምስት የይዘት አሰልጣኞች $339,000፤
- በት/ቤት የተመሰረተ የመምህራን አመራር እና የሰራተኛ እድገት ለማቀናጀት/ለማቀላጠፍ 15 የስራ ቦታዎች ለመጨመር $1.1 ሚልዮን፤
- ከትምህርት ጊዜ ውጭ የInterim Instructional Services (የጣልቃ ትምህርት አገልግሎቶች) ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አገልግሎቶችን ለማሻሻል፣ ስድስት ቦታዎችን ጨምሮ፣ $255,550
- የአትሌቲክ አሰልጣኝ አገልግሎት ለሁሉም ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለማቅረብ $329,000፤
- ተጨማሪ የአመራርና አስተዳደራዊ ድጋፍ በሁሉም የትምህርት ክፍሎች ለማቅረብ ከ$834,000 በላይ እና $600,000 አካባቢ የሚደርስ በኤኮኖሚ ቀውስ ወቅት ለጠፉ የመምህራን ቦታዎች ለመተካት፣ እና
- የኮሌጅ ምዝገባና ውድድር ለሚንከባከበው ለAchieving Collegiate Excellence and Success (ACES) $250,000፣ እና ችግር ላላቸው ልጆች ለመርዳት ለChildren's Trust (የልጆች በጎ አድራጎት) $250,000።